# ኢትዮጵያዊ ዜግነት እንጅ

## ኢትዮጵያዊ ማንነት የለም!

ጽሑፉ ሦስት ዓበይት ርዕሶች የያዘ ሲሆን በይዘቱም የኢትዮጵያ የፖለቲካ ችግር ነቅሶ ያትታል፤ መፍትሔ ሃሳቦችንም ይጠቁማል። መልካም ንባብ!

ዲ/ን ሙሉጌታ ወልድገብርኤል
ጥቅምት 18/2013
አሜሪካ

# ክፍል ፩

## ትናንት አንድ አልነበርንም! ዛሬም አንድ አይደለንም! ለወደፊቱም አንድ ልንሆን አንችልም!

ከተራ ጭኸትና መፎክር ያላለፈ፤ መያዣና መቸበጫ የሌለው፤ ልብ አውልቅ፤ ባለቤት ያጣ፤ ግልጽ የሆነ ራዕይና ግብ የሌለው፤ የተዘበራረቀና የተምታታበት፤ አይደለም ሰፊው ሕዝብ ለአንድ ዓላማ ሊያሰልፍ፣ ሊያሳምንና አግባብቶም ከጎኑ ሊያስከትል ቀርቶ እርስ በርስ መስማማትና መደማመጥ ያቃታቸው የሥመ ፖለቲከኞቻችን አስቀያሚና አሳፋሪ መልክና ምንነት እንደተጠበቀ ሆኖ በተለያዩ ምክንያቶች በሚነሱ ጊዜያዊ ኃይማኖታዊና ማኅበራዊ ጥያቄዎችና አለመግባባቶች እንደ ባልቴት እየተለጠፍክና እየተንጠላጠልቅ ሕዝብ እንደ መሰላል መወጣጫ በማድረግ ምኒሊክ ቤተ መንግሥት ዘው ብለህ ለመግባትና የሥልጣን ሁሉ ባለ ቤት ለመሆን የሚደረገው ሩጫና ጥድፊያ ሳስበው ኢትዮጵያውያን እስከ ዳግም ምጽዓት ድረስ የሚያስፈልገን ሳናገኝ እንዲሁ እንደጮህን፣ እንደናፈቀንና በሰው አገር ኢምባሲ እንደ ብቅል እንደተሰጣን እንዳናልፍ ነው የምፈራው።



### የጽሑፉ ዓላማ፥

ጽሑፉ በይዘቱ ቀለል ያለ፤ በጣም በስሱ የተዘጋጀ ሲሆን የጽሑፉ ዓላማ ደግሞ ሀገር ወዳድ ዜጎች ለማወያየት ታስቦ የተጠመረ ጽሑፍ ነው። ጽሑፉ ምንም እንኳ በይዘቱም ሆነ በአቀራረቡ ከወትሮ ቀለል ያለ ቢሆንም ምድራችን አሁን ለምትገኝበት የተመሰቃቀለ ገጽታ መፍትሔ ሐሳብ በማበርከት/በመጠቆም ረገድ የራሱ ሚና ይጫወታል ተብሎ ይታመናል።

### ማሳሰቢያ፥

አንባቢ ሆይ! ይህን ታሪካዊ ማንነታችን አንስቼ ለመወያያ ሳቀርብ የሕዝቦች ልብ ለመክፈል ሳይሆን የጽሑፉ ዓላማ በሚል ንኡስ ርዕስ ሥር ግልጽ በሆነ ቋንቋ ለመግለጽ እንደተሞከረ አገር ካንጃበበባት አደጋ ለመታደግ እንደ አንድ ዜጋ ግዴታዬን መወጣቴ መሆኑ ይታወቅ ዘንድ ስጠይቅ በአክብሮት ነው።

## ሐተታ፥

### ትናንት ...

በህይወቴ የሚከብደኝ ነገር ቢኖር ስለ ትናንት [ስለ ስላልነበርኩበት] ዘመን መናገር ነው። በተለይ ታሪክ ነክ ጉዳዮች አንዳንድ ጊዜ ከአረጊቶች ተረት ባልተናነሰ መልኩ እንደ ደራሲው/ጸሐፊው ዝንባሌ፣ ውስጣዊ ምኞት/ፍላጎትና ተልዕኮ በአጠቃላይ ታሪክ ነክ ትረካዎች ከሐቁ እጅግ ርቀው ጸሐፊው እጅ ላይ የወደቀ ሆኖ የምናገኝበት አጋጣሚ ጥቂት አይደለም። በተለይ በብዙ ነገር ወደኋላ የቀሩ አገሮች የታሪክ መዛግብት አያያዝና ሳይከለስ፣ ሳይሰረዝ፣ ሳይበረዝና ሳይደለዝ በአግባቡ ከትውልድ ወደ ትውልድ በማስተላለፍ ረገድ ተአማኙነቱ እስከዚህም ነው። እንዲህ ዓይነት ወጥነት የጎደለበት የእርስ በርስ የታሪክ መጣረስና መፋለስ እውን የሚሆንበትምና የሚፈጠርበትም አንድ ራሱ የቻለ ምክንያት አለው።

ቀላል ምሳሌ ላንሳ። ይኸውም፥ የኢትዮጵያ ታሪክ የተመለከትን እንደሆነ [ኢትዮጵያ በስምምነት ሳይሆን በሃይል የተመሰረተች አገር ናት የሚለው አስተሳሰብና አመለካከት እንደተጠበቀ ሆኖ] በአሁን ሰዓት በምስራቅ አፍሪካ ቀንድ የምትገኝ ኢትዮጵያ ተብላ በምትታወቅ አገር ስር የተጠለሉና የታቀፉ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ስለ ምድሪቱ ወጥ የሆነ

ታሪካዊ አስተሳሰብም ሆነ አመለካከት የላቸውም። የኢትዮጵያ ታሪክ በአማራ ተወላጅ ጸሐፊ ያለው ሚዛን በኦሮሞ ወይም በትግራይ ተወላጆች እንዲሁም በሌሎች ብሔር ብሔረሰቦች የታሪክ ጸሐፊዎች ያለውን ሚዛን አንድ አይደለም።

ምሳሌው ያጠበብነው እንደሆነ "አከራካሪ" የምኒልክ ታሪክ ለተነሳ ርዕስ ጥሩ ምሳሌ ነው። በአማራ ተወላጆች የታሪክ ጸሐፊዎችና ተናጋሪዎች ዘንድ ምኒልክ ማለት ጀግና፣ የተዋጣለት የዲፕሎማሲ ሰው፣ የሰለጠነ፣ ቆፍጣና መሪ ሲሆን በኦሮሞና በትግራይ የታሪክ ጸሐፊዎችና ተናጋሪዎች ዘንድ ደግሞ ምኒልክ ጀግና መሆኑ ይቀርና ምኒልክ ማለት አረመኔ፣ የእናት ጡት ቆራጭ፣ ቅጥረኛ ነፍሰ ገዳይ፣ ግፈኛ፣ ዘራፊ፣ ከሐዲ (እምነት የሌለሽ)፣ ቤተ ክርስቲያን ሳይቀር የሚዘርፍ ወመኔ፣ ሐሞት የሌለው ሽንታም፣ ሀገር ለባዕዳን አሳልፎ የሸጠ ባንዳ … ወዘተ ዓይነት ሰው ሆኖ ነው የምናገኘው።

በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ "ምኒሊክ ማን ነው? ምን ዓይነት ሰው ነበር? (ግለ ሰብእናው?) የአመራር ብቃቱ? ፖለቲካዊ አስተዳደር (አገዛዙ) ምን ይመስል ነበር? ከበቀለበት ብሔር ውጭ ከሌሎች ብሔር ብሔረሶች ጋር የነበረው ግኑኝነት ምን ይመስል ነበር? ማወቅ እፈልጋለሁ።" ብሎ የምኒሊክ ታሪክ ለማጥናትና ለማወቅ የሚጓጓ ሰው ካለ፤ ቻይናውያን "መንገድ ከመጀመርህ በፊት ለከፉም ለደጉም ደርሰው የተመለሱትን ጠይቅ" እንዲሉ በበኩሌ ለዚህ ሰው ለፍለጋው ስኬታማነት የምመክረው ምክር ቢኖር አንድም ምኒልክ በአካል አግኝቶ መጠየቅ ነው ይህ ካልሰራ ደግሞ በምኒሊክ ዘመን የነበረ ለነፍሱ ያደረ አረጋዊ ሰው አግኝቶ እንዲያነጋግር ብቻ ነው ምክሬን የምለግስለት። ከዚህ ያለፈ በምኒሊክ ዙሪያ የተጻፉ መጻህፍት አገለባብጬ እውነቱን እደርስበታለሁ ማለት ግን ከቅዠት ያለፈ ሌላ ምንም ሊሆን አይችልም። ከንቱ ልፋት ነው የሚሆነው። ተጻፉ የሚባሉ መጻህፍት ፉት አድርጎ እንደጨረሰ የተጨበጠ ነገር ስለማያገኝባቸው ዙሮ ዙሮ በምኒሊክ ዘመን የነበረ ሰው ፍለጋ መምጣቱ አይቀርምና። ይህ የምልበትም በቂ ምክንያት አለኝ።

በነገራችን ላይ 2013 ዓ/ም ላይ ሆኖ ስለ ምኒልክ ደግነት፣ ወንድነት፣ አርቆ አሳቢነትና ጀግንነት ሽንጡን ይዞ የሚጮህና የሚሞግት ሰው ሆነ ስለ ምኒልክ ነውራምነት፣ ሌብነት፣ ቅጥፈት፣ ወገበ ነጭነትና ባንዳነት የሚጽፍና የሚያወራ በምኒልክ ዘመን የነበረ የዓይን እማኝ (ቅሪት) ሆኖ ሳይሆን ማንበብ የሚፈልገው (በአወገንተኝነት ወይም ለልዩ ተልእኮ የተጻፉ) ብቻ እየመረጠ አንብቦ እንጅ ሌላ ምስጢር የለውም።

ጸሐፊው የአማራ ደም ካለበት ስለ ምኒልክ ቢጽፍ ደግ ደጉን ነው የሚጽፈው። በአንጻሩ ደግሞ ጸሐፊው ከአማራ ብሔር ውጭ የሌላ ብሔር ተወላጅ የሆነ እንደሆነ ደግሞ (የኦሮሞ ሊሆን ይችላል ከትግራይ ሊሆን ይችላል ከደቡብም ሊሆን ይችላል) ከሞላ ጎደል ስለ ምኒሊክ ተቃራኒው ነው የሚጽፈው። የውጭ ዜጎች ጸሐፍት እንደሆኑም አዝነውልን ሳይሆን ራሱ የቻለ ተልዕኮ ያላቸው ሰዎች ናቸው። የምክሬ መሰረትም ይህ ነው። ታሪክ ሂሳብ አይደለም። ታሪክና ሕልም እንደ ፈቺው (እንደ ጸሐፊው) ነውና። ስለ ሌሎች አጼዎችና ነገሥታትም እንዲሁ። ታድያ ይህ ሁሉ የሚያሳየው አንድነታችን ሳይሆን ልዩነታችንን መሆኑ እውቅና ሊሰጠውና ሊሰመርበት የሚገባ ጉዳይ ነው። ለችግሮቻችን እውቅና በመስጠት ነውና ትክክለኛ መፍትሔ ልናገኝ የምንችለው።

ሌላው የአሁኒቷ ኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት "የምኒሊክ ቤተ መንግሥት" ተብሎ መጠራቱና መታወቁ ታሪካዊና ፖለቲካዊ አንድምታው ምን ዓይነት መልክዕክት እንዳለውና እንደምያስተላልፍስ አስበውበት ያውቃሉ? ለጥያቄው በቂና ምክንያታዊ ምላሽ ካልዎት ማንነትዎና ታሪክዎ ጠንቅቀው የሚያውቁ፤ ስለ ተባለና ስለተነገረ ብቻ የማይደነባበሩ፤ ከነፈሰ ጋር የማይነፍሱ ጭምት ሰው ኖት ማለት ነው። እንግዲያው ለእርስዎ አንድ ባንዴራ ያልነበረን፤ የዛሬ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦችም ራሳቸው የቻሉ የራሳቸው ሥልጣኔና ታሪክ የነበራቸው መንግሥታት እንደነበሩ ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ ብሎ አንድ አገር ወይም አንድ ሕዝብ የሚባል እንዳልነበረ ይህች በቂ መልዕክት ናት።

ዛሬም … !

የኢትዮጵያ ነባራዊ የፖለቲካ ሁኔታ በማስመልከት "ለኢትዮጵያውያን" ለመናገር መድፈር ለቀባሪ እንደመርዳት ነው የሚሆነው። አሁን ስለ ምንገኝበት ሁኔታ ብዙ ለማለት መሞከርም በእውነቱ ነገር የአንባቢያን ጊዜ ማባከንና አንባቢን ማሰላቸት ነው የሚሆነው። የኢትዮጵያ ችግር በቅጡ አጥርቶ ማየት የተሳነው ዜጋ ያለ እንደሆነ፤ ወይንም የኢትዮጵያ ጉዳይ ይመለከተናል የሚሉ ድረ ገጾችና ሚድያዎች የሚያስተጋቡት ጽምጽ እውነት መስሎት የኢትዮጵያ ችግር የዲሞክራሲ፣ የፍትህ ወዘተ ችግር ነው ብሎ የሚያምን ሰው ካለ ከዚህ ቀደም "ኢትዮጵያ፡ ጨወታ ለማሳመር የምትመዘዝ ጆከር ናት!" በሚል ርዕስ ለንባብ የበቃ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ችግር የሚጠቁም በማንበብ በቂ ግንዛቤ ያገኛል የሚል እምነት አለኝ።

በአጭሩ ጥያቄዎቻችን የፈለግነው ቀለማት እየቀባባን ሌላ መልክ ለመስጠትና ለማስያዝ ብንሞክርም "ኢትዮጵያውን" አሁን በዚህ ዘመን የምንገኝበት አሳፋሪ ሁኔታ (ፖለቲካዊ) አንድነታችን የሚያሳይ ነው የሚል ካለ አእምሮውን የጣለ ሰው ብቻ ነው። ትናንት አንድ እንዳልነበርን ሁሉ ዛሬም አንድ አይደለንም። ሰው የሚያየው ጎሳን መሰረት ያደረገ ግጭቶቻችንና ንትርኮቻችን የልዩነቶቻችን ምልክት/ነጸብራቅ ነው።

"ጥሩ ውሀ የጥቅምት ነበርሽ ማን በጠጣሽ፤ ጥሩ ምክር የደሀ ነበርሽ ማን በሰማሽ!"

አሁንም "አዎ! አንድ አልነበርንም።" ወደሚለው መሰረታዊና ታሪካዊ ማንነታችን ልንመጣ ይገባል። በመቀጠልም በጠመንጃ ሳይሆን በጠረጴዛ ዙሪያ ላይ ተቀምጠን ኢትዮጵያ ተብላ የምትታወቅ ሀገርም ሆነች ኢትዮጵያዊ ተብሎ የሚታወቅ ሕዝብ የተዳፈነ ማንነት ያለን ሕዝቦች እንጅ አንድ ሕዝብ እንዳይደለን እናስምርበት። [ይህን ስል ምን ለማለት ተፈልጎ እንደሆነ በሚቀጥሉት ተከታታይ ጽሑፎቼ ሰፊ ማብራሪያ እሰጥበታለሁ] ይህን ስናደርግ ወደሚፈለገው ሁሉን በጋራ የሚያሳትፍና ተጠቃሚ የሚያደርግ አገር ገንብተን በሰላም በፍቅርና በመጠባበቅ መኖር ያስችለናል። ይህን ባናደርግ ግን በመግቢያዬ እንደጠቀስኩት "የኢትዮጵያ ሕዝብ/ኢትዮጵያዊ" ተብሎ መጠራቱ ቢያምንበትም ባያምንበትም ሰዎች የኢትዮጵያ ፓስፖርት እስከያዙ ድረስ የምድሪቱ ስም በተነሳ ቁጥር ከርታታ ሕዝብ ተብሎ መታወቁ ይቀጥላል። ትናንት የነበረ ዛሬም ያለ መቆራቆስና ፍጭትም ይቀጥላል። ምን ነው? ቢሉ የያዘም አይለቅም የተያዘም አርፎ አይቀመጥምና። ጥበብ በጎዳና ላይ ትጮሃለች!

ጎበዝ! ታመናል። መታመማችን ደግሞ አምነን እንቀበል ዘንድ ይገባናል። መታመማችን አምነን መድሃኒት ፍለጋ ከተነሳን ደግሞ ለህመማችን መድሃኒት እናገኝ ዘንድ ህመማችን አፍረጥርጠን ልንናገር ይገባል። ይህ ደግሞ ምርጫ ሳይሆን ግዴታ ነው። አፍ አውጥተን ችግሮቻችን መናገር ያቃተንና እንቢ! ያልን እንደሆነ ግን "በሽታውን የደበቀ መድኃኒት የለውም" እንደሚባለው ህመማችን አፍ አውጥተን እስከምንናዘዛት ድረስ ከነበሽታችን እየተሰቃየን መኖራችን ግድ ነው።

## በጽሑፉ ቅሪታ ላላችሁና ለተሰማችሁ ግለሰቦች፥

<u>የሲያል ፈላስፋ ፕሬዝዳንት ኢሳይያስ አፈወርቂ ኢትዮጵያን ለመበታተን የኢትዮጵያ ታሪክ አስመልክተው በሰነዘሩት አስተያየት ተስማምተው ሲያበቁ እኔ ስለ ሀገሬ ለመፍትሔ ይሆን ዘንድ በፍቅር እውነት ነው ብዬ የማምንበት መናገር ሆነ መጻፍ የማልችልበት ምክንያት እንዲነግሩኝ ብቻ ነው የምጠይቀት። በጸሐፊው ሃሳብ አለመስማማት መብትዎ ሆኖ ኢትዮጵያ ተከፍላ ለሁላችን እኩል የምትደርሰን አገር እስከሆነች ድረስ ሃሳብን በሃሳብ ከመቃውም ያለፈ ሌላ ስም የመለጠፍም ሆነ የመስጠት ማንም መብት አለው ብዬ አላምንም። የመቃወም መብት እንዳሎት ሁሉ እኔም በሥርዓቱ የመጻፍ መብት አለኝ።</u>

* * *

# ክፍል ፪

## “ኢትዮጵያውያን” በምናችን ነው አንድ የሆነው? አንድማ አይደለንም!

### የጽሑፉ ዓላማ፥

ውጫዊ ማንነታችን (ልዩነቶቻችንን) ሕጋዊና ተገቢ የሆነ እውቅና በመስጠት እንደ ሕዝብና እንደ ሀገር ቀጥ አድርጎ ሊያቆመን የሚችል ውስጣዊ ሕብረትንና ውህደትን መፍጠር እንችል ዘንድ ተጻፈ።

### ሐተታ፥

አንድ አንድ ነው። በንድፈ ሃሳብ ደረጃም ሆነ በመርህ ደርጃ ወይም መሬት ላይ ባለው ሐቅ የአንድ ሁለት የለውም። አንድ አንድ ነው። አንድ ሲደመር አንድ ሁለት። አንድ ሲካፈል ለአንድ አንድ ነው። ከራሱ ጋር ከተባዛም ራሱ አንድ ነው። ከተቀናነሰ ደግሞ ዜሮ ነው። ውህደትን በተመለከተ ሊኖረው የሚችለው ትርጉም ግን በመጠኑም ቢሆን ለየት ያለ ነገር አለው። ለዚህም ጥሩ ምሳሌ ሊሆነን የሚችለው መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጋብቻ የሚናገረውን ቃል ነው።

“ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ በሚስቱም ይጣበቃል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ” ይላል (ዘፍ. 2፥24፤ ኤፌ. 5፥ 31)። “ይጣበቃል” እንዲል ጋብቻ (መጋባት/ውህደት) ማለት ምን ማለት እንደሆነ መናገሩ ሲሆን “አንድ ሥጋ” ሲል ደግሞ በባልና በሚስት መካከል ያለውና ሊኖርም የሚገባው እርስ በርስ የመሸካከም፣ በነገሮች ሁሉ የመቻቻል፣ የመስማማት፣ የመደማመጥ፤ የመናበብ ወዘተ በአጠቃላይ ልዩ ቁርኝት፤ አንድ ልብ፤ አንድ ሃሳብ መሆንን የሚያመላክት በባልና በሚስት መካከል ያለ የረቀቀ የግኑኝነት/ውህደት ጥልቅ ትርጉም የሚገልጽ ነው።

ይህ በባልና በሚስት መካከል ያለውን ግኑኝነት ሊፈርስ የሚችልበት ሁኔታ በተመለከተም መጽሐፍ ቅዱስ የሚከተለውን ይላል “እኔ ግን እላችኋለሁ፥ <u>ያለ ዝሙት ምክንያት</u> ሚስቱን ፈትቶ ሌላዪቱን የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል” እንዲል ከሁለቱ አንዳቸው ከትዳር ውጭ/ከሌላ ሰው ጋር ግብረ ስጋ ግኑኝነት (ዝሙት) የፈጸመ እንደሆነ ብቻ ትዳራቸው ሊፈርስ ወይም ሊበተን እንደሚችል ያስረዳል።

### “አሃዳዊነት” ‘Vs.’ “ብዙሐዊነት”፥

“አንድነት” በሀገራዊ ጉዳይ ላይ ሊኖረው የሚችል ትርጉምና ይዘት  አንስተን እጅግ በጥቂቱ “የአንድነት” ወይም “የውህደት” ትርጉም የተመለከትን እንደሆነ “አሃዳዊነት” አንዱ የውህደት ወይም የአንድነት አይነት ሲሆን ይኸውም፥ ወተትና ውሃ አንድ ላይ መቀላቀል እንደማለት ነው። ይህ ዓይነቱ ውህደት ደግሞ በኢትዮጵያ ምድር ፈጽሞ ዳግም እውን ሊሆን የማይችል፣ ተቀባይነት የሌለው ከመሆኑም በላይ ግልጽነትና ፍትሐዊነት የጎደለበት፣ ሚዛኑ የተዛባና አድሉዓዊ ውህደት ለመሆኑ በበቂ ሁኔታ  ካለፉ ሥርዓቶች ታሪክ ለመማር ችለናል።

ሌላኛው የአንድነት ወይም የውህደት ዓይነት ብዙሐንን የሚያሳትፍ ለጊዜው በአማርኛ “ብዙሐዊነት” እንበለው ይኸውም፥ ዘይትና ውሃ አንድ ብርጭቆ ውስጥ እንደማስቀመጥ ማለት ነው። ማንም በማንም ላይ ሳይሰለጥን፤ አንዱ ሌላውን ሳይውጥና ሳያጠፋ፤ ዘይት ዘይትነቱን ውሃ ደግሞ ውሃነቱ እንደጠበቀ የሚፈጥሩት እኩልነት ላይ የተመሰረተ ፍትሐዊና ሚዛናዊ አንድነት፣ ውህደት፣ ወይም ህብረት ማለት ነው።

## በምናችን ነው አንድ የሆነው?

"ኢትዮጵያ" እንደ አገር ከቆመችበትና ከተመሰረተችበት ጊዜ አንስቶ እስከ ወታደራዊው የደርግ ዘመነ መንግሥት መደምሰስ ያለውን ጊዜ አንዱ በሌላው ላይ የበላይነቱ የሚያሳይበት አሃዳዊ ሥርዓት ስትናጥ የመጣች አገር ስትሆን የኢህአዴግ መንግሥት ወደ ሥልጣን ከመጣበት ያለውን ጊዜ ጀምሮ ደግሞ ከሞላ ጎደል ኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች ራሳቸው በራሳቸው የሚያስተዳድሩበት ብዙሐንን ያሳተፈ ፌዴራላዊ ስርዓት የዘረጋች አገር ሆና እናገኛታለን።

ታድያ ቀዳሚ ጥያቄአችን የሚሆነው እውን "ኢትዮጵያውያን" አንድ ነን? የሚለውን ጥያቄ መመለስ ይሆናል። የዛሬይቱ ኢትዮጵያ በጥቂቱ ትግራይ፣ አማራ፣ ኦሮሞ፣ ሶማሊ፣ ጋምቤላ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ የደቡብ ሕዝቦች፣ አፋር፣ ሃራሪ … ተብለው የሚታወቁ ልዩ ልዩ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ድምር ውጤት ናት። እንግዲህ እነዚህ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በምን ሂሳብ ነው አንድ ሊሆኑ የሚችሉ? በምናችን ነው አንድ የሆነው? የኢትዮጵያ ሕዝብ ማለት "የፋብሪካ ሳሙና" አይደለም። እንደው "አንድ ነን!" ተብሎ ስለ ተጮኸም "አንድ ነን" ማለትም አይደለም።

"የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ ነው!" ሲባል አባባላችን በተጨባጭ አስደግፈን ማስረዳት መቻል፣ በቂና ምክንያታዊ ምላሽ መስጠት አለብን። በምናችን ነው አንድ የሆነው? እግር ኳስ ወዳጆች ኳስ ሜዳ ወጥተን አንድ ባንዴራ ስላውለበለብን? ለጦርነት አንድ ላይ ስለዘመትን? በነገራችን ላይ ለጦርነት መዝመት አንድነታችን የሚያሳይ ከሆነ እርስ በርስ ስንተላለቅበት የኖርን ዘመን ሆነ አሁን ያለው ድምጽ አልባ ቀበሌ ተኮር ጦርነትስ ምን ሊባል ነው? የአንድነት መገለጫ? እንዲህማ አንቀልድ።

- ስማችን ልዩ ልዩ፤
- ቋንቋችን ልዩ ልዩ፤
- ባህላችን ልዩ ልዩ፤
- ታሪካችን ልዩ ልዩ፤
- አስተሳሰባችን ልዩ ልዩ፤
- የኑሮ ዘያችን ልዩ ልዩ፤
- አመጋገባችን ልዩ ልዩ፤
- አኗኗራችን ልዩ ልዩ፤
- ማኅበራዊ ሥርዓቶቻችን/እሴቶቻችን ልዩ ልዩ፤
- ወግና ልምዶቻችን ልዩ ልዩ፤

ቀደም ብለን በዝርዝር የተመለከትናቸው ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በምንም ዓይነት መመዘኛ አንድ ሊሆኑ አይችሉም አይደሉምም። [አንድና ሁለት አንድ ናቸው በማለት ሳይንሳዊ ያልሆነ ሙግት አንስተን መነታረክ ካላማረን በስተቀር] ሀገራዊ አንድነት በውጫዊ ማንነት አይለካም የሚል ዝሩው ፍልስፍና ለማስተጋባት ብንሞክር እንኳ "ኢትዮጵያውያን አንድ ነን!" በማለት አፋችን ሞልተን ለመናገር እንደ ሕዝብ አንድ ዓይነት አስተሳሰብና አንድ ዓይነት ልብ አለን ወይ? ነው ጥያቄው፤ የለንም። ቢኖረን ኖሮ ጥያቄው ራሱ እንደ ጥያቄ ለማንሳት ባልተገደድን ነበር። አንድነት ምንድ ነው? ለማለት የተገደድንበት ዋና ምክንያትም ሌላ ሳይሆን አንድነት ስለሌለን ነው።

ጎበዝ! የአቢስንያ ሆነ የኢትዮጵያ ታሪክ የእርስ በርስ ግጭት፣ የመላላጥና የጦርነት ታሪክ ነው። የለም! የሚል ካለ ደግሞ "አቢስንያ/ኢትዮጵያ" ተኘታ ያደረችበት ዘመን በጭብጥ አስደግፎ ይቅረብ። ካልሆነ ግን ሐቁ ታሪካችን የጦርነት ታሪክ ነው። ጦርነት ደግሞ የአንድነት ምልክት ሊሆን አይችልም። ጦርነት የልዩነት መለያ ነው። ተግባብተንም ሆነ አንድ ሆነን አናውቅምና። እንደው ይህ ሁሉ ውስጣዊም ውጫዊም ልዩነት ኑሮን ብንግባባ ነበር የሚደንቀው።

## አንድ ልብ ወይስ አንዲት ባንዴራ?

አንድ ልብ ካለን በአንዲት ባንዴራ ስር ተጠለልን አልተጠለልን ምንም ለውጥ አይኖረውም። አንድ ልብ ኖሮን በአንዲት ባንዴራ ሥር የመጠለልና የየራሳችን ባንዴራ የማውለብለብ ነገር የምርጫ ጉዳይ ነው የሚሆነው። ሰው አንድ ልብ፣ አንድ ሃሳብ፣ አንድ ግብና አንድ ዓላማ እስካለው ድረስም  በቁጥር እልፍ ቢሆንም ምን ጊዜ አንድ ነው። አንድ ልብ ሳይኖረን አንድ ባንዴራ ብናውለበልብ ግን ራስን ከማታለል አልፎ ሌላ ምንም ሊሆን አይችልም።

አንድ ባንዴራ ስላውለበለብን አንድ ነን ማለት አይደንም። ጎበዝ! አንድ ባንዴራ ማውለብለቡ ቀርቶብን አንድ ልብ ኖሮን የየራሳችን ባንዴራ እያውለበለብን በሰላም ተፋቅረንና ተዋደን ብንኖር አይመረጥም ወይ? እንደው እየተበጣበጥን ከመኖር መቶ እጥፍ ነው የሚሻለው።

መቼም የሐበሻ ዘር ስንባል ሁሌ ራሳችንን ከሰው አገር ማነጻጸር አይደል የሚቀናን እንግዲያውስ ኢትዮጵያ ከአውሮፓ ህብረት አገራት ምን ትማራለች? ብሎ መጠየቅና ከአውሮፓ ህብረት አገራት ተመክሮ መቅሰም ጥበብ ነው። አንድ ባዴራ ኑሮን ሲያበቃ አንድ ልብ መሆን ካቃተን እንደ አውሮፖ “ለአርባ አራት” ተበጣጥሰን የየራሳችን መንግሥት መስርተን የየራሳችን ባንዴራ እያውለበለብን አንድ ልብ ብንሆን/ቢኖረን ነው የሚሻለው። ጭቅጭቅ የሌለው ጠቅላይ ሚኒስትሩም፣ ምኑም ምኑም በወንዝዎ ልጆች ቁጥጥር ስር ሆኖ ራስዎን በራስዎ ስያስተዳድሩ። አይመስሎትም? ሁከትና መበጣበጥ ምን ዋጋ አለው ብለው ነው።  ሰላም ማውረድና መፍጠር የምንችልበት ብዙ ምርጫዎች እያሉን ለምን በሆነ ባልሆነ ስንጨቃጨቅ ውድ ጊዜያችንን እናጠፋለን? ኧረ ወዲያ! ተበጣጥሰን ማደግ ከተቻለ ተበጣጥሰንም ቢሆን እንሞክረው። ታድያ ተመራርቀን። (ለበለጠ ለምን ተለያይተንም ቢሆን አንሞክረውም? ያንብቡ)

## አንዱ ሌላውን የሚፈልግበት ምሥጢሩ ምንድ ነው?

“አንድነት/ኢትዮጵያ” ሲባል ሌላ መታለፍ የሌለበት ጥያቄ ቢኖር አንድነቱ ያስፈለገበት ምክንያት/ምሥጢሩ ምንድ ነው? ለሚለው ጥያቄ ግልጽ የሆነ መልስ መቀመጥ አለበት ባይ ነኝ። ሲዳማው፣ ጋምቤላው፣ ሶማሌው፣ አፋር … የኢትዮጵያ ክፍል ሆነው እንዲቀጥሉ የሚገደዱበት ምክንያት ምንድ ነው? የእነዚህ “አናሳ” ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መብትና ስልጣን እስከ ምን ድረስ ነው? ለምንድ ነው የምንፈልጋቸው? በኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ እኩል እንደ አማራው ትግሬና ኦሮሞ የማይሰለፉ ከሆነ ለምንድ ነው የምንፈልጋቸው? ምሥጢሩ ምንድ ነው? በእኩልነት ስለምናምን ነው ወይስ አሁንም በአንድነትና በባንዴራ ስም ለመጨፍለቅ፣ ለማሸት፣ ያለ ልክ ተጠቃሚዎች ለመሆን፣ ታላቅነታችንን ለማስመስከር ነው? ለመሆኑ በእንዲህ ዓይነት የድብብቆሽና የውሸት አንድነት በምትመሰረት አገር አትራፊው/ተጠቃሚው ማን ነው? ትናንት ሁሉም እኩል ተቋዳሽ እንዳልነበረ በታሪክ ያየነው እውነታ ነውና። ኢትዮጵያዊ ነህ እያልክ ከምትገድለኝ “ኢትዮጵያዊነት” ቢቀርብኝስ? [አይቀርብኝም እንጅ! ልብ ይበሉ፡ ኢትዮጵያውነት ዋጋቢስ ነው አላልኩም። መልዕክቴም አይደለም] አይመስሎትም? ወይስ በኢትዮጵያዊነቴ መንገሥተ ሰማያት እገባለሁ ብለው ያምኑ ይሆን? ብሎ የሚያምን አይኖርም አይባልም ብቻ ግን አይጣል ነው።

አንባቢ ሆይ! እርስዎስ ምን ይላሉ? እያንዳንዱ የራሱን ይዞ በራሱ በመቆም ፈንታ ለምንድ ነው አንዱ ከሌላው ጋር መኖር የፈለገው/የሚፈለገው ይላሉ? ተፈጥሮአዊ ነው ብሎ ስለሚያምን? ትልቁ “አናሳውን ብሔር” ስላዘነለትና ስለራራለት? ወይስ አማራ ያለ ትግራይ፣ ያለ ኦሮሞ፣ ያለ ደቡብ … ወይም ትግራይ ያለ አማራ፣ ያለ ኦሮሞ፣ ያለ ደቡብ … እንዲሁም ኦሮሞ ያለ ደቡብ፣ ያለ አማራ፣ ያለ ትግራይ … ወይም ደቡብ ያለ ኦሮሞ፣ ያለ ትግራይ፣ ያለ አማራ … “መሸቶ አይነጋልኝም!” ወይም “ህይወት አይኖረኝም!” ብሎ ስለሚያምን ነው? ወይስ በውስጠ ወይራ አንዱ ሌላውን ለመመዝበር ነው?

ይብዛም ይነስም ሁሉም እኩል የሆነ መብትና ሥልጣን ከሌለው አንዱ ሌላውን የሚፈልግበት ምክንያት ምንድ ነው? ምሥጢሩ ምንድ ነው ይላሉ? ለዚህ ጥይቄ የሚመለከታቸው አካላት በተለይ በአሃዳዊ ስርዓት የተለከፉ መልስ መስጠት አይጠበቅባቸውም ብለው ያምናሉ? ወደድንም ጠላንም ተድበስብሰንና ተሸዋውደን የምንኖርበት ዘመን አብቅተዋል። ትውልድ አልፎ ትውልድ በተተካ ቁጥር እርስ በርስ እንደተበጣበጥን ለመኖር ምርጫ ካላደርገን በስተቀር አንዱ የበላይ አንዱ የበታች ብሎ ፖለቲካ ሊኖር እንደማይችል ለሁላችን ግልጽ ሊሆን ይገባል።

ምን እናድርግ? (ነጥቦቹ ለመወያያ በተነሳ ርዕስ ዙሪያ ብቻ የሚያጠነጥኑ ናቸው)

- ለችግሮቻችን እውቅና እንስጥ። [የኢትዮጵያውያን ችግር የብሔር/የጎሰኝነት ችግር ነው!]
- ልዩነታችንን አምነን እንቀበል። [ምንም በታሪክ አጋጣሚ "ኢትዮጵያዊነት" የሚል መሰጠሪያ ብንይዝም ኢትዮጵያ የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ደምር ውጤት መሆንዋን፤ ሁሉም (የብሔር ብሔረሰቦች ማለቴ ነው) እኩል መብትና ሥልጣን እንዳለው አምነን እንቀበል።]
- ግልጽነት ይኑረን።
- ለጋራ ጥቅም፣ ኢኮኖሚ፣ መከላከያ፣ ከረንሲ ... ወዘተ የሚሉትን መደለያ ቋንቋዎች ትተን አንድነት የተፈለገበት ዋና ምክንያት በግልጽ እናስቀምጥ።
- ዘለቄታ ያለው ሰላም መፍጠር የሚቻለው በኃይል ሳይሆን ምርጫ ላይ የተመሰረተ መሰባሰብ እንደሆነ አምነን እንቀበል።
- አሃዳዊነት አገር የሚበትን ጨቋኝ ሥርዓት እንጅ አገር እንደማያቆም እንመን።
- ብዙሐኑን ያሳተፈ ሚዛናዊና ፍትሐዊ እኩልነት ላይ የተመሰረተ የጋራ አገር ለመገንባት አሮጌ አስተሳሰብ እንሻር።

* * *

# ክፍል ፫

## ኢትዮጵያዊ ዜግነት እንጅ ኢትዮጵያዊ ማንነት የለም!

### የጽሑፉ ዓላማ፥

ጽሑፉ በይዘቱ አብዛኛዎቻችን አፍ አውጥተን እንድንናገረው የማንፈልገው ርዕሰ ጉዳይ የሚዳስስ ሲሆን ዓላማው፥

አንደኛ፡ የምድራችን መሰረታዊ ችግር መጠቆም፤

ሁለተኛ፡ ከነ ልዩነቶቻችን ሁሉን እኩል ተጠቃሚ የሚያደርግ አንድነት መፍጠር እንደሚቻል ለማበረታታት፤

ሦስተኛ፡ ኢሳትና በመሳሰሉ አንዳንድ የጎሳ ዜማ አቀንቃኝ ድረ ገጾች ከምን ጊዜም በላይ አንድን ሕዝብ ያነጠጠረ የከፈቱት የጦርነትና የጥላቻ ዘመቻ ከወዲሁ ይታሰብበት ዘንድ ለማሳሰብ ተጻፈ።

### ጥብቅ ማሳሰቢያ፥

- ጽሑፉ በማንነት ዙሪያ የሚያጠነጥንና የሀገራችን የፖለቲካ ችግር የሚጠቁም እንጅ ብሔር ተኮር አጀንዳ የለውም። እንዲህ ያለ እንቅስቃሴም አያበረታታም። የጽሑፉ ዓላማ ከሚለው ሥር ግልጽ በሆነ ቋንቋ ከሰፈረው ውጭ ሌላ ምንም ዓይነት ዓላማ እንደሌለው በድጋሜ ለማሳወቅ እወዳለሁ።
- የጽሑፉ ርዕስ ስያሜ፥ የሀገራች ሥር የሰደደ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣና በአሁን ሰዓት ትልቁም ትንሹም በማዋረድ ያለውን ጎሳ ማዕከል ያደረገ ፖለቲካ የሚያመላክት እንጅ ርዕሱ የጸሐፊው ግላዊ ድምዳሜ አይደለም።

### ሐተታ፥

የኦሮምያ ክልል ተወላጆች በማንነቱ ኦሮሞ ለሆነ ሰው ያላቸውን አስተሳሰብና አመለካከት ከሌላ ብሔር ለሆነ ወገን ማለትም ለአማራ፣ ለትግራይ፣ ለደቡብ ያላቸውን አስተሳሰብና አመለካከት ሲነጻጸር አንድ አይደለም። አማራ ወገኔ የሚለውን ከአማራ ነገድ የሆነውን ሰው በሚያይበት መነጽር የትግራይ፣ የኦሮሞ፣ የደቡብ … ተወላጆችን እኩል አያይም። የትግራይ ተወላጆችም እንዲሁ የራሴ የሚለውን የትግራይ ሰው በሚያይበት መነጽር የአማራ ክልል ወይም የኦሮሚያ ክልል ተወላጅ … እኩል አያይም።

- በግልጽም በስውርም እያፋጀን ያለው የማንነት (የብሔርተኝነት) ጥያቄ ነው። [የብሔር ጥያቄ ማንሳት በራሱ ኃጢአት ነው እያልኩ አይደለም። ለጥያቄው የሚሰጠው መልስ ላይ ነው የእኔ ትኩረት]
- አንድ ማንነት ቢኖረን ኖሮ አንዱ አንዱን ለመግደል ባላሴረና ባልተሳ ነበር።
- ታሪካችን የመገዳደል ታሪክ ነው። ከዚህ ታሪክ ጀርባ ያለው ታሪክ ደግሞ  የማንነት ጉዳይ ነው። ዛሬም ቢሆን አቅም ታጥቶ ነው እንጅ ሰዎች ተኝተው ስላደሩ አይደለም።
- ኢትዮጵያውያን የአንድ ማንነት ባለቤቶች ብንሆን ኖሮ እዚህ ሁሉ ችግር ውስጥ ባልገባን ነበር። ጥያቄአችን በዲሞክራሲ፣ በፍትሕ፣ በሰብዓዊ መብት ወዘተ ሽፋፍነን አሳመርነው እንጅ ጥያቄአችን የማንነት ጥያቄ። ባይሆን ኖሮ ችግሮቻችን ለመፍታትና ለመደማመጥ ባልተሳነን ይህን ያህልም ባልተቸገርንና ነበር።
- የኢትዮጵያ ችግር የሚፈታ ፖለቲካዊም ሆነ ሌላ አማራጭ መንገድ ታጥቶ አይደለም። ታድያ ጥያቄው “ማን ይሁን የበላይ?” ነው። ለነገሩማ ማንስ የበታች መሆን ይወዳል ብለው ነው። እንግዲያውስ መሬት ላይ ያለው ሐቅ ይህ ነው።

ኢትዮጵያዊነት በፓስፖርት የሚለካ ከሆነ የኢትዮጵያ ስም ሲጠራ ቅሬታ ያላቸው አንዳንድ የኦሮሚያ ክልል ተወላጆች ጨምሮ በፓስፖርት ደረጃ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ነው። በማንነት ደረጃ ግን ቀደም ሲል እንደተገለጸው ነው። ማንነት በደፈናፍ እንዲህና እንዲያ ነው ተብሎ የሚታለፍ አልያም በመፎክርና በጭሆት የሚገለጽ ሳይሆን ማንነት የሚታይ፣ የሚጨበጥ፣ የሚዳሰስ፣ ወጥነት ያለው፣ የሚገለጽ፣ አንዱ ከሌላው ተለይቶ የሚታወቀው ልዩ መታወቂያ ነው።

ማንነት "ሰው ሰራሽ" አይደለም። ማንነት "ተፈጥሮአዊ" ነው። አንዱን ብሔር ከሌላኛው ብሔር የሚልዩ ነጥቦች (ለምሳሌ፡ ቋንቋ፣ ባህል፣ ታሪክ፣ አስተሳሰብ ወዘተ) እንዲሁ የሰው ማንነት መገለጫ ናቸው። ኢትዮጵያውያን የጋራ ቋንቋ፣ የጋራ ባህል፣ የጋራ ታሪክና አስተሳሰብ እስከሌለን ድረስ ደግሞ የጋራ ማንነት ሊኖረን አይችልም። የችግሮቻችን ምንጭም ይህ ነው።

ጎበዝ! ፍጥጥ ያለ እውነታ በመካድ ወይንም በማዳፈን የሚመጣ ለውጥ የለም። በምድሪቱ ፈውስ ሆነ መሰረታዊ ለውጥ እንዲመጣ ከተፈለገ መቀበል ያለብንን እውነታ በመቀበል እንጅ ከእውነታው በመሸሽ አይደለም። ለምሳሌ ኢትዮጵያ የራሳቸው መገለጫ ማንነት ያላቸው ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ድምር መሆንዋን በምርጫ ሳይሆን ይህን ሐቅ የመቀበል ግዴታ እንዳለን በማመን ሐቁን በሐቅነቱ ልንቀበል ይገባናል። ከዚህ ሐቅ በሸሽን ቁጥር ግን በስህተት ላይ ስህተት እየሰራን እንደሆነም ሊታወቅ ይገባል።

## "ኢትዮጵያዊነት" ምንድ ነው?

ኢትዮጵያዊነት ክብር! ኢትዮጵያዊነት ኩራት! ኢትዮጵያዊነት ፍቅር! ኢትዮጵያዊነት ...! ወዘተ አይደለም የእኔ ጥያቄ። ጥያቄው በኢትዮጵያ ታሪክ የት ቦታ ነው ብሔር ብሔረሰቦች በኢትዮያዊነታቸው ተጠቃሚ የሆኑት? ምድሪቱ "ኢትዮጵያ" የሚል ስያሜ ከያዘች አንስቶ በማን ዘመን ነው ብሔር ብሔረሶች ተጠቃሚዎች የሆኑ? ጥቅማ ጥቅሙ ቀርቶባቸው ህልውናቸውስ በውል ይታወቅ ነበር ወይ? "ነት" የሚለውን አነጋገር መደለያ ቋንቋ ከመሆኑ አልፎ ያስገኘለት ጥቅም ምንድ ነው? እንደ ኢትዮጵያዊ ከሌላው ትልቁ ኢትዮጵያዊ ጋር ሲነጻጸር ኢትዮጵያዊነት የሚያስገኘው ጥቅማ ጥቅም እኩል ተካፋይና ተቋዳሽ ነበር ወይ? ነው ጥያቄው። መልሱ አልነበረም ነው። ስለዚህ "ኢትዮጵያዊነት" ምንድ ነው? ኢትዮጵያዊስ ማን ነው? ለሚለው ጥያቄ አጥጋቢና ምክንያታዊ የሆነ ምላሽ መስጠት ይጠበቅብናል። እንግዲያውስ ግልጽነት ሆነ ለችግሮቻችን መፍትሔ ከዚህ ነው የሚጀምረው።

## "ኢትዮጵያዊ" ማን ነው?

ትግራዋይ – ትግራዋይነቱን ትቶ፣ አማራ – አማራነቱን ትቶ፣ ኦሮሞ – ኦሮሞነቱን ትቶ፣ ሀረሬ፣ አፋር፣ ደቡብ ... ሌሎችም እንደዚሁ የየራሱ ልዩ ማንነት (መታወቂያ) ትቶ "ኢትዮጵያዊ" ተብሎ ይጠራና ይታወቅ ዘንድ የተፈለገበት ምክንያት ምንድ ነው? ኢትዮጵያዊነት እርስ በርስ መጨራረስ ከሆነ "ኢትዮጵያዊ" መባል የሚያስገኘው ልዩ ጥቅም ምንድ ነው? ቻይናዊ? ኢትዮጵያዊ ተብሎ ባለ መጠራቱ ምን ቀረበት? ሁከትና ጦርነት።

ኢትዮጵያ መፍረስ አለባት እያልኩ አይደለም። አላልኩም። አላልኩም። ስለ ኢትዮጵያ አሉታዊ አመለካከት እያንጸባረቅኩም አይደለም። ኢትዮጵያ ለእኔም አገሬ ናት። የእኔ ጥያቄ፥

- ኢትዮጵያውነት እኩልነት ካልሆነ፤
- ኢትዮጵያዊነት ፍትሐዊነት ካልሆነ፤

- ኢትዮጵያዊነት እያንዳንዱ ብሔር ብሔረሰብ “ትልቁም” “ትንሹም” የምድሪቱ በረከት እኩል ተካፋይ የማያደርግ ካልሆነ፤ [ምን ጥግ ጥጉን ያስኬደናል፡ በታሪክ የምናውቃት ኢትዮጵያ ለአንዱ እናት ለእንድ ደግሞ የእንጀራ እናት ናት።]
- ኢትዮጵያዊነት የብሔር ብሔረሰቦች የማንነት ጥያቄ የማይመልስ ከሆነ፤
- ኢትዮጵያዊነት የብሔር ብሔረሰቦች የፖለቲካዊ፣ የኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ነጻነት ዋስትና የማያረጋግጥ ከሆነ፤ ኢትዮጵያ የምትባል አገር እንድትኖር የተፈለገበት/የሚፈለግበት ምክንያት ምንድ ነው?
- ኢትዮጵያዊነት አንዱ የበላይ አንዱ የበታች ማለት ከሆነ ኢትዮጵያ የምትባል አገር በመኖርዋ/በህልውናዋ ተጠቃሚ የሚሆነው ማን ነው?ኢትዮጵያዊነት በቀጥታም በተዘዋዋሪም አንድን ሕዝብ እየነጠልቅ ማጥቃት ማለት ከሆነ ኢትዮጵያ! ኢትዮጵያ! ከሚለው ጩኸትና ሽለላ ጀርባ ያለው አንጀንዳ ምንድ ነው? ይህ የምለው ከመሬት ተነስቼ አይደለም። ሳትወለድ የተጨናገፈች ሀገር መሪ የሆኑት የሲያል ፈላስፋ ፕሬዝዳንት ኢሳይያስ ኢትዮጵያን አስመልክተው የሰነዘሩት ቃል ምስክሬ ነው። ራሱን ከፈጣሪ ማስተካከል የሚቃጣው የሙብት ሕጋዊ ትርጉም የማያውቅ “የሰብዓዊ” መብት ተሟጋች፣ ሥመ “ጋዜጠኛ”፣ “አክቲቪስት” ወዘተ ሀገር ስትገሸለጥና ሕዝብ በቁሙ ሲሸለት ምን አሉ? አገሬ ለሚላት ኢትዮጵያ ምን አደረገላት? ሕዝቤ ለሚለው ሕዝብስ? ባዶ። በኢትዮጵያዊነቱ ለድርድር የማይቀርብ ሕዝብ ለመዝለፍና ለማዋረድ ግን ተኝተው አላደሩም። [በነገራችን ላይ እነዚህ “የሰብዓዊ መብት ተሟጋች”፣ “ጋዜጠኛ”፣ “አክቲቪስት” ወዘተ የሚሉ ተቀጽላዎች አንድ ሰው በዳይስፖራ የጥላቻና ዝሩው ፖለቲካ ሲጠመቅ በገጸ በረከት/በቸርነት ያለ ወረፋ የሚሰጡ “የክርስትና” ስሞች ናቸው።]

ሌላ “የማይገባኝ” ነገር፡ አንዱ ሌላውን “የለም! ተነጥለህና ተገንጥለህማ የራስህን መንግሥት ማቆም አትችልም።” ሲል የሚሞግትበት ምክንያት ምንድ ነው? መገነጣጠሉ፣ መለያየቱና መነጣጠሉ ሁላችን የማይበጅ ጎጂ ነው ተብሎ ስለሚታመን ነው (እንዳልሆነማ አውቃለሁ) ወይስ ሌላ ምክንያት አለው? ብሔር ብሔረሰቦች ማንነታቸውን አጥተውና ተረግጠው በምትገነባ አገር ተጠቃሚ የሚሆን ማን ነው? ይህም በግልጽ መቀመጥ አለበት። ይህ ትውልድ የራሱ የሆነ ነገር አሳልፎ የማይሰጥ የሌላውንም የማይፈልግ ትውልድ ነው። እንዴት ነው ነገሩ? እስከ መቼ ነው ትውልድ በባንዴራ ሽፋን ማንነቱ ያጣ ዘንድ የሚገደደው። “አባቴ” መግዛት ተችሎ ይሆናል እኔና “ልጄ” ግን በመቃብራችን ላይ መቆም ይቻል እንደሆነ ብቻ የማውቀው።

<u>በተረፈ ጸሐፊው፥ ከነ ልዩነቶቻችን እንዴት አንድነት መፍጠርና አስተማማኝ፣ ዘለቀታዊ ሰላም ያላት፣ ዜጎች በማንነታቸው አንገታቸው ቀና አድርገው የሚሄዱባት፣ የብሔር ብሔረሰቦች እኩል ፖለቲካዊ ተሳትፎ ያላት፣ የበለጸገች አንዲት አገር (ኢትዮጵያ) መገንባት እንደምንችል ብንመካከርና ብንፈላለግ ነው የሚሻለው ይላሉ እርስዎስ?</u>

D/n Mulugeta Weldegebrial

Email: yetdgnayalehe@gmail.com

United States of America

Oct 18, 2013